**የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር**
**(ኢ.ብአግ)**

**Ethiopian National United Front**
**(ENUF)**

---

## በቅንጅት መሪዎችና በሌሎች ኢትዮጵያውያን ላይ በሻዕቢያዊ ወያኔዎች የተወሰነውን ፖለቲካዊ ሕገ-ወጥ ብይን አጥብቀን እናወግዛለን

### የወያኔ 3ፕሮግራም4 ፍርድ እብደት ወይንስ እብሪት?
### ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

ዛሬ በኢትዮጵያና አካባቢዋ የወያኔ እብደትና እብሪት ተደራርበው፣ የሻዕቢያው ወያኔ/ማሌሊት በኩረ-አባቶች ድጋፍና ችሮታ ተደምሮበት ውድ ሀገራችን ለዘለዓለማዊ ኋላ ቀርነት፣ ሕዝቧም ወደማያባራ ጦርነት፣ ሰቆቃ፣ በሽታና ድህነት አዘቅት እየወረደ ታዘግማለች።

ለዚህ አባባላችን ተጨባጭ መረጃዎች የሚሆኑት ከዚህ በፊት አቶ መለስ ዜናዊና ደቀ መዛሙርቱ አዘጋጅተው ያሳተሟቸው መጽሓፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ እንዲሁም ዲስኩሮች በተለይም፣ መሪዎቹ ያደረጓቸው የመድረክ ንግግሮች ናቸው። የሻዕቢያዊ ወያኔዎች መጽሐፍ ቅዱስ 3የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት? የምትለዋ ድግምት ናት። አሁን ደግሞ እንደ አንድ ተጨባጭ ምሳሌና ማስረጃ ማቅረብ የሚቻለው የወናኔ ፈጣሪና ቀንደኛ መሪ የሆነው አቶ ስብሃት ነጋ በቅርቡ ያስተላለፈው መልዕክት ነው። የወያኔው የንስሃ አባት ስብሃት ነጋ ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በዓይጋ የወያኔ ፎረም ላይ የሰጠውን ቃለመጠይቅና ያደረገውን ንግግር የሰማ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለ ሕወሓት እና ስለ ማሌሊት (ማርክሲስት ሌኒንስት ሊግ ትግራይ) አመሠራረትና ማንነት ሊረዳ ይችላል።

የአቶ ስብሃት ነጋ ንግግር በእውነቱ እብደት ወይንም ጭፍን እብሪት መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም። አነጋገሩ እብደት ነው ለማለት የሚያስደፍረው እውነትም ሕሊናውን ያልሳተ ሰው የማሰብ ኣዕምሮ ካለው፣ ተጨባጭ ነገርን ክዶ፣ ጉም በመጨበጥ ወደ ቅዠትና ዓይን ያወጣ ውሸት ያዘቅጣል ብሎ ማመን አስቸጋሪ ይሆናል። እብሪት ነው ለማለት የሚያደፋፍረው የስብሃት አጥፍቶ መጥፋት ምኞት፣ ፍላጎት፣ ሂደትና ልምድ፤ 3አህያ እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል አለች4 እንዲሉን ያስታውሳል።

ማንያህሎኝነት፣ አጉል መኩራራት፣ ከአቅም በላይ መንጠራራት፣ ተራ የውንብድና ተግባርን ማዳነቅና ማጋነን፣ መመፃደቅንና የሰው ደም አፍስሶ መደንፋት፤ በቅጥፈት ሳይነኩ ድረሱልኝ ብሎ እሪታ፣ እንደ ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል/ያለቅሳል መሆኑ አያጠራጥርም። በአድዋ ከተማ እንደቀልድ የተጀመረው የመንደር ሌብነት፣ ወደመቀሌ ባንክ ዘረፋ ዘልቆ፣ የእምዬ ሚኒልክ ቤተመንግሥትን ብዝበዛ አስከተለ። የሕዝብ ንቀትና እብሪታዊ ምጽቀት ወደ ፉከራና ሽለላ ተመነዘረ። መዋሸት፣ እኩይነት፣ ጭካኔ፣ ተገለባባጭነትና ምላስን ማጠፍ እንደ ሙያ ተቆጠረ። 3በጎጠኞችና በኢሕአዴግ መሃል እርቅ የሚባል ነገር የለም4 ተባልን። 3በአስተያየት ልዩነት እስካለ ማንም ከማንም ሊታረቅ አይችልም፤4 ተብሎ ታወጀ። ይህ የእብደትና የእብሪት ጉዞ በማርና መርዝ ተለውሶ ፀረ-ኢትዮጵያዊነትን ፀንሶ ወለደ። ለዚህ ነው ከዚህ በፊት ባደረግነው ንግግርና ባወጣነው መግለጫዎች ወያኔ ከሃዲ ድርጅት ስለሆነ ሊታረም፣ ሊለወጥ፣ ሊመከር፣ ሊሻሻል፣ የሚችል ድርጅት አይደለም ብለን ያሳሰብነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሰው የ፲፯ ዓመት ግፍና ሰቆቃ ጊዜውን ጠብቆ የሚገፈፍ ሲሆን ክህደት፣ ባንዳነትና ራዕየ-ቢስነት ግን ምንጊዜም ታርክን ሊፍቁ አይችሉም። ይህ የእስቲ ኑና ይዋጣላችሁ እብሪት ለፍልስጤማውያን፣ ለሩዋንዳውያን፣ ለዩጎዝላቮችና ለኢራቆችም አልፈየደም። የኢ.ብአግ ራዕይና የትግል ስልት ይህን ሁሉ ያገናዘበ ነው። አሁንም በድጋሜ ለወገናችን ማሳሰብ የምንፈልገውና አስቀድመን የምናስጠነቅቀው፣ አቶ ስብሃት ግልጽ አድርጎ እንዳስቀመጠው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው ምርጫ ለአንዴና ለመጨረሻው ሀገሩን ለማዳንና ነፃነቱንና መብቱን ለማስከበር ቆርጦ መነሳት እንዳለበት ነው። የሕዝቡን አልሞት ባይ ታጋይነት ወኔ

---

**P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A. •**
**Telephone (202) 785-1618**
**www.enufforethiopia.org**

በመስበር፣ ፋይዳ በሌለው የምስለኔዎች አማላጅነትና ንትርክ፣ የላም አለኝ በሰማይ ክርክርና እርስ በርስ ፉክክር ጊዜን ማባከኑ የሕዝቡን ሰቆቃ ማራዘም ነው።

ሻዕቢያዊው ወያኔ መታረም፣ መሻሻል፣ መለወጥና መጋለጥ አይችልም። ሕሊና ቢስና ሞራል-ብልሹ የሆነ፣ ከአፈጣጠሩ ተጣሞ፣ ተወላግዶና አጎብድዶ የሚራመድ ሥርዓት ወይም በወያኔ አነጋገር 3ፕሮግራም4 በፀሎት፣ በፍትሃት፣ በልመና፣ በድርድርና በግርግር ብቻ ሊወገድ አይችልም። እነ አቶ ስብሃት ነጋ በመሣሪያ አፈሙዝ የነጠቁትን ሥልጣን በምንም ተዓመር እንደማይለቁ አረጋግጠዋል። እንዲያውም አቶ ስብሃት፣ ሌሎች የሱን ምስያዎች ለመፍጠር በትጋት እየሠራ መሆኑን አስጨብጦናል። አንድ አሽከር ጎባጣ ጌታውን ተከትሎ አጎብድዶ ሲሄድ ያየው ወዳጅ ምነው ጎበጥክ ቢለው፣ አሽከርዮው ጌታዬን ለመምሰል ነው አለ ይባላል። ይህ የወያኔ የጥፋት ዛቻና ዘመቻ አሁኑኑ ካልተቀጠፈ እነዚህን አጎብዳጅ ካድሬዎችና አዲስ የሚኮተኮቱትን ጠማማ ችግኞችን መልሶ ለማቃናት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከባድ ሸክምና ሀገሪቱም በቀላሉ ልትወጣው የማትችለው ዕዳ ይሆናል።

ሻዕቢያዊው ወያኔ በቅንጅት አመራር አባላት ላይ ባለፉት ሁለት ዓመታት የፈፀመውን የሰብአዊ መብት ገፈፋና ሕገ-ወጥ ውሳኔ የታዘበ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የወያኔን ማንነት በሚገባ ስለተረዳ፣ ከዛሬ ጀምሮ በመወናበድ ወይንም አውቆም እራስን ደልሎ ሌላውን በማደናገር በኢትዮጵያ ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት በሠላም ተመስርቶ፣ እርቀሠላም ወርዶ፣ የልማት እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ ዕድገት ዳብሮ ወደ ሀገር ልማት ጎዳና ለመሄድ የሚቻል አስመስሎ መዋዠቅ እራስን ለወያኔ ሰላባነት አመቻችቶ ማቅረብና ሕዝብን ለባርነት መዳረግ ይሆናል።

በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን የጋራ የሀገር ጉዳዮች ላይ ተወያይተን የሕዝብን ፍላጎት እናሟላ ተብሎ ለወያኔ በተደጋጋሚ ልመና ሲቀርብ፣ ወያኔ የሰጠው መልስ የአስተሳሰብ ልዩነት በመካከላችን ስላለ እኛ ያልነውን ካልተቀበላችሁ ጊዜአችንን አታጥፉ ነው። ወያኔዎች ሊግቱን ያዘጋጁልን መርዝና የደደቢቷን የጠንቋይ እትብት አንግተን፣ እጃችንን ሰጥተን ለዘላቂ ባርነት እንድንዳረግ ያለሙትንና ያሰላሰሏቸው ጽንሰ ሃሳቦች፣ ምክንያቶች ምንድን እንደሆኑ የስብሃትን ግንግር ያዳመጠ ሁሉ በቀላል ሊረዳ ይችላል። የስብሃትን ዲስኩር በዝግታ ሙሉ ንግግሩን ለማዳመጥ እንድትችሉ ከዓይጋ ፎረም ያገኘነውን ቅጅ በድረገፃችን ላይ አስቀምጠነዋል። እንዲሁም ከዚህ በታች ያለውን መገናኛ በማጣቀስ መስማት ይቻላል።

ቃለመጠይቅ ክፍል፩ ቃለመጠይቅ ክፍል፪ ቃለመጠይቅ ክፍል፫ ቃለመጠይቅ ክፍል፬

አንባብያን በመሠረቱ ስብሃት ነጋ ኦፌሴላዊ አቋም ነው ብሎ የተነተናገራቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ከንግግሩ ውስጥ ቀንጭበን የተነተናቸው ሲሆን ሙሉ በሙሉ የራሱ ቃላት የሆኑትን በቅንፍ ውስጥ አስቀምጠናል።

1. አቶ ስብሃት እንዲህ ይለናል። በኛ ምኞትና ፍላጎት ላይ ተመርኩዘን የምትታነፀው አዲሲቱ ኢትዮጵያ 3ከአሮጌዋ4 ኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት ተመሳሳይነትና ግንኙነት የላትም። 3አሮጌዋ ኢትዮጵያ በኃይል አንድ እንድትሆን ተይዛ ነበር።4 የኛዋ አዲሲቱ ኢትዮጵያ ግን የተገነባችው በሕዝቦች እኩልነት ያለው አንድነት ላይ ነው። መጀመሪያም ገና መንቀሳቀስ ስንጀምር በቂ አቅም አይኑረን እንጂ ራዕያችን ይኸው ነበር። የኛን ራዕይ አዲስ አበባው ኮንፈረንስ ላይ ለሌሎቹ ነፃ አውጪዎች ለማስረዳት ስንሞክር ከባድ ፈተና ገጠመን። ሌሎቹ የሚፈልጉት መገንጠል ስለነበረ እኛ 3አብረን እንኑር በእኩልነት ስንል ሁሉም ተገረሙ።4 ስለዚህ 3ሕገ-መንግሥታችንን እንዲቀበሉ ለማድረግ ከባድ ሸክም ሆኖብን ነበር። በመሆኑም 3በግንቦት ፳ ቀን የኢትዮጵያ አንድነት [እኛ ባናድነው ኖሮ] አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችል ነበር።4 አሁንም 3ብሔርተኝነት አያዋጣም። መሰበር አለበት።4 3እኛ ታጥቀን የተነሳነው ጭቆናን

ለማርገፍ ነበር።4 የኢትዮጵያ ታሪክ እየተባለ የሚዘከርበት 3አሮጌው nationalism [ሀገር ወዳድነት] ድንበር መጠበቅ ብቻ ነበር። የኦርቶዶኮስ ሃይማኖት የnationalism መሠረት ሊሆን አይችልም። ያንን ይዞ መቀመጥ አይቻልም። አዲሱን nationalism ለመገንባት ከባድ ነው። ግን ለኛ ምንም አያዳግተንም። ድንበር ማስከበሩን ግን አዲሱ nationalism ይቀጥላል።4

2. የእኛ አመራርና ድርጅታችን ከቀሩት ነፃ አውጪ ድርጅቶች የተሻለ ራዕይ የነበረውና አሁንም ያለው ከመሆኑም በላይ ሌሎች ነፃ አውጭዎች የኛን ያህል መስዋእትነት አልከፈሉም፤ ሊከፍሉም ቢመኙ ብቃት የላቸውም። ስለዚህ ድሉና ግኝቱ የኛ ብቻ ነው። እኛ ሳንሆን እነሱ ናቸው የብሔር ድርጅቶች። 3ሁሉም የብሔር ድርጅቶች እንጂ 'multinational' [በኅብረ-ብሔር የተደራጁ] የሆኑ አልነበሩም።4 የኦሮሞ፣ የሱማሌ፣ የሲዳማ ወ.ዘ.ተ. ነፃ አውጭዎች ወደ ስህተት ጎዳና ያመሩትና የሚሸነፉትም የኛን 3ፕሮግራም4 ተቀብለው ሥራ ላይ ባለማዋላቸው ነው። ኤርትራን ነፃ አውጥተን ነፃነት ከሰጠን በኋላ እነ ኢስያስ አፈወርቂ 3ፕሮግራማችን4 ባለመከተላቸው ወደ አዘቅት ወርደው ሕዝብን አደኸዩ፤ አስፈጁ።

3. የኤርትራም ሕዝብ የሚፈልገው እኛ በቀረው ኢትዮጵያ የጎሳ ክልሎች ያዳበርነውን ዓይነት 3ዴሞክራሲ4 ስለሆነ እነ ኢሳያስን ሕዝቡ አስወግዶ 3ፕሮግራማችን4 እዚያም ሥራ ላይ ይውላል። በአንድ በኩል፣ የሻዕቢያ መሪ [አቶ ኢሳይሳ] አሁን ያለውን መንግሥት [ወያኔን] ለመተካት ምኞት አለው። በማያዋጣ military invincibly [እብሪተኛ አልበገሬ ጦረኝነት] ተመክቶ እሱ ያለውን ብቻ በግድ ተቀበሉ ይለናል። እጃችሁን ስጡ አለን። በሌላው ወገን ደግሞ እነ ስዬ አብርሃና ገብሩ አሥራት 3ለትግራይ በቂ ልማት አልተደረገም፣ ለኤርትራ ተንበረከክን ይሉናል። አደናጋሪ መሪ [ኢሳያስ] ለብዙ ጊዜ አይቆይም።4 እኛን ግን ማንም ሊያደናግረን አይችልም። ኤርትራን ከኢትዮጵያ ቅኝ ተገዥነት ለማላቀቅ ከሕወሓት የበለጠ የተዋጋ ኃይል የለም። ወደፊትም ኤርትራ ብትነካ ለመከላከል ዝግጁ ነን።

4. 3ፕሮግራማችን4 boundary [ወሰን] የለውም።4 ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሱማሌና ለቀረው አፍሪቃ ልማትና እድገት አማራጭ የሌለው መሆኑ ታምኖበት በምሳሌነቱ ተቀባይነት አግኝቷል። 3ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች በፕሮግራማችን ያምናሉ።4 "We have a stake in it አሉ።4

5. እኛ 3ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለናል።4 3የወሓት ፕሮግራም ብቻ ነው ትክክለኛው።4 በእውቀት፣ በጥበብና በተጨባጭ የትግል ስልት የተገኘውን 3ፕሮግራም4 አንግበን፣ የጦር መሣሪያ አጠቃቀምን ተክነን፣ ሁሉንም ተቀናቃኝ ድል መትተን ሥልጣንን ጨብጠናል። የኢትዮጵያን ሕዝብ በትረ-መንግሥትና ሥልጣን ለመያዝ የቻልነው በእግዚአብሔር እርዳታ ወይንም በመሣርያ ኃይል ሳይሆን ሕዝቡ 3ፕሮግራማችንን4 እንዲቀበል በዘዴ ስላስተማርነው ነው። 3ሳንተኩስ ነው በቀጥታ የገባነው። አዲስ አበባ ስንገባ በታንክ አልነበረም። ታንኩ አጃቢ ነበር።4 3ፕሮግራማችን ነው በቀጥታ አዲስ አበባ ሊያስገባን የቻለው።4 3ፕሮግራማችን4 የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ ይውጣ ነው የሚለው።4 የቀሩት ነፃ አውጭዎች ትልልቆች ነበሩ። 3ግን የኛን ራዕይ አንዳቸውም ከቁም ነገር አልቆጠሩትም። የኤርትራ ትግል ትክክል ነው ብለን ያመንን እኛ ብቻ ነበርን። በዚህ ምክንያት፣ ከሻዕቢያ በስተቀር ሁሉም ሲያዋክቡንና ሲወጉን ነበር። ከጀብሃ ሁለት ዓመት፣ ከኢሕአፓ ሶስት ዓመትና ከኢዴኅ ጋር ሁለት ዓመት ተዋግተናል።4

6. አሁን ይህ 3ፕሮግራማችን4 በሕገ-መንግሥታችን ተቀርጾና ሕያው ሆኖ እንዲኖር አቅደናል። ይህ ሕገ-መንግሥታችን ምናልባትም አስፍላጊ ሆኖ ሲገኝ ሊሻሻል ይችል ይሆናል እንጂ በምንም ተዓምር ሊለወጥ አይችልም። በመሆኑም 3ሕገ-መንግሥታችንን4 ለማፍረስ ሙከራ ተደርጎ ምናልባትም እኛ

ከሥልጣን ብንወርድ ኢትዮጵያ ትፈራርሳለች። 3ሕገ-መንግሥቱ የሚሻሻል እንጂ የሚለወጥ አይደለም።4 ሕገ-መንግሥታችን ከተነካ 3የኢትዮጵያ አንድነት ይፈርሳል።4 ሕገ-መንግሥታችን የማይከበር ከሆነ 3ኢትዮጵያ overnight [በአንድ ምሽት] ነው የምትገነጣጠለው።4 3መጀመሪያ ትግራይ፣ ቀጥሎ አፋር ይሄዳል።4 3ይህ constitution ከተነካ የኢትዮጵያ አንድነት የሚባል ነገር የለም ብያለሁ። ሕገ-መግንሥታችንን በንቃት ነው የሠራነው። ማነነታችን ስለሆነ አንቀማም ማንነታችንን። ይህን የሚያደናቅፍ ከመጣ እንገነጣጠላለን። ከተቀማን ጦርነት እናውጃለን። ሁላችንም መንደር እንይዛለን። ወደ መንደራችን ተመልሰን ልምድ ስላለን እንደገና እንንቀሳቀሳለን። (ለማንኛውም ከአዲስ አበባ በስተቀር አሁን ሁላችንም በየመንደራችን ነው ያለነው።) Constitution ይህን ማንፀባረቅ አለበት።4

7. 3የኤርትራ ፌዴሬሽን ባይፈርስ ፴ ዓመት ጦርነት አይነሳም ነበር።4 ዛሬ 3የኢትዮጵያ ሕዝብ አይትቶ የማያውቀው አዲስ ሥርዓት (institutions) መሠረትን። 3የኢትዮጵያ ሕዝብ የመወሰን መብት አገኘ። [የጎሳ] የክልል አስተዳደር ለዚህ ነው ያስፈለገው።4

8. ከተቀናቃኞቻችን ጋር ያለውን በተመለከተ 3ዋናው ጉዳይ "issue" ነው እንጂ ሰው ማየት የለብንም። ስለዚህ ውይይታችንን ከመለስ [ዜናዊ] አንጀምር። በሀገር ጉዳይ ላይ እንጀምር። ጡረታ ለምን አትወጣም የተባለው እኔ ማንነቴ ዘላቂ ነው፤ ከሥልጣን ጋር አይገናኝም። እኔ እራሴን "indispensable" [አማራጭ የማይገኝለት] ማድረግ አልፈልግም። እኔ "redundant" [ከጥቅም ውጭ] አልሆንኩም። ግን ድክመቴ አምስት ስድስት እንደኔ የሆኑ [የወያኔ ቡችሎች] በፍጥነት አላመረትኩም። ማምረት አለብኝ። ያኔ እኔ "useless" [ከጥቅም ውጪ] እሆናለሁ።4 ሁኔታውን ስንመለከት ግን የምናየው 3እያንዳንዱ የሚታገለው ኢሕአዴግን [ወያኔን] ለማጥፋት ነው።4 እኛ ግን ያጋጠመንን እንቅፋት እንደ ስርቅታ በማየት በሚያኳራው የጦር ኃይላችንና እንከን የለሽና ጥበብን የተላበሰ የፖለቲካ ዓላማና ክነት በመጠቀም የተነሳብንን ተቃውሞ ሁሉ ሙሉ በሙሉ አውድመናል።

9. ቅንጅቶች ቀርበው ለመከራከር አልፈለጉም። 3መፈንቅለ መንግሥት አቅደውና መርተው ሕገ-መንግሥቱን ለመድፈር ሞከሩ።4 የ2005 ምርጫ ለኛ ፈተና ነበር። ከምርጫው በኋል እስር ቤት የገቡት በአመለካከት ነበር። Constitution የማፍረስ አመለካከት። በማያዳግም መንገድ እስር ቤት መግባት ነበረባቸው። ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥልጣን በመንገድ አይቀማም። እስራኤሎች እንዳሉት never again። በአመለካከት ላይ reconciliation የለም። አፈርና ወርቅ [reconciliation] ማድረግ አይቻልም። ምህረት ግን ሊሰጥ ላይሰጥ ይችላል። እርቅ የሚባል ነገር የለም። ማንና ማን ነው የሚታረቀው። በጎጠኞችና በኢሕአዴግ መኃል እርቅ የሚባል ነገር የለም።4

ወገን ሆይ፤

ይህ ከላይ የተዘረዘረው የወያኔን እብሪት፣ ቅሽበት፣ ቅዠት፣ ትዕቢትና ቅጥፈት በማያጠራጥርና በማያዳግም ግልጽነት ቀርቦ ሳለ፣ ዓይናችንን ጨፍነን፣ ጆሮአችንን ዘግተንና ምላሳችንን አጣጥፈን፣ ከወያኔ ጋር እንደራደር ማለታችን፣ ታላቁ መሪያችን አርበኛው ሳይንቲስት ዶ/ር ቅጣው እጅጉ እንዳለው ሁሉ፣ የወያኔን ማንነት የማናውቅ ሞኞች እኛ ነን ወይንስ ወያንኤዎች የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ ተገደናል። በስብሃይ ነጋ እብሪት ተቆጭተን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብና የሀገሪቱን ዳር ድንበር ጠባቂ ሠራዊትና አርበኞች ይህን ጉዳይ አጢነው አስፈላጊውን የሀገር ማዳን እርምጃዎች እንዲወስዱ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
(ኢ.ብአግ)

Ethiopian National United Front
(ENUF)

የምናቀርበው ጥያቄ ትዕግስቱ እስከ መቼ ነው? ምንድንስ ነው የምንጠብቀው? የተሰጠን መልስ በቂ አይደለም ወይ? የኢትዮጵያ ጀግኖች የሐሰት ክስና ደደቢት ላይ የተተበተበ መረጃ ቀርቦባቸው ለሁለት ዓመትታ ታስረው ሲማቅቁ፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች አድኑን እያሉ እየጮሁና ወደ 3አፍሪቃው ጓንታናሞ (African Guantanamo) ሲጋዙ፤ ከ፪፻ በላይ የሚሆኑ ሠላማዊ ሰልፈኞች በጠራራ ፀሐይ በአደባባይ ሲረሸኑ፤ በእየክፍለ ሀገሩ በገሃድና በስውር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ደም በከንቱ ሲፈስ፤ እናቶች ልጆቻቸውን ለማዳን እሪ በማለታቸው በጥይት ሲቆሉ፣ ምዕመናን በየቤተክርስቲያናቱ አድባራትና መስጊዶች ሲታረዱ፣ ሕዝብ የመረጣቸው የፓርላማ ተወካዮች ፍትሕ በጎደለው ውሳኔ እስራትና የሞት ቅጣት ሲፈረድባቸው፤ ጋዜጠኞች አንደበታቸው ተጋርዶ አፋቸው ሲለጎም፤ ትምህርት ቤቶች ዳሽቀውና ተዘግተው ወጣቱ ሥራ አጥቶ ሲጉላላ፤ አልሞት ባይ ተጋዳዮች በየበረሃው ሲንከራተቱ፣ ደሃ፣ አርሶ አደሩና ሥራ አጡ ወጣት ቦዘኔ ተብሎ ሲወነጀልና ሲታፈስ፤ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የኔ ብጤው በበሽታ፣ በችጋርና በረሃብ ተሰቃይቶ ሕይወቱ ስታልፍ አይተን እንዴት እንዳላየ እንሆናለን?

ኸረ ለመሆኑ፣ በራስ የማይተማመንና ኢትዮጵያን የካደ መለስ ዜናዊ ባዘጋጀልን አሳዛኝና ዘግናኝ ትያትራዊ ድራማ የሶስተኛውን ሺህ ዓመት ዋዜማ ከሱ ጋር ለማክበር እንዴትስ ተብሎ ይታሰባል። መለስ ከገባበት ማጥ ውስጥ ለመውጣት ሲል ይዞ የሚጨብጠውን ሲያጣ አሁን የሁለት ሺህ ቲያትር አመጣ። እንዴትስ ተገምቶ አቶ መለስ ትላንት የተፈጠረች፣ አንድ መቶ ዓመት ያልሞላት ኢትዮጵያ እያለ በማፌዝ፣ ድንበሯ እንኳን የት እንደሆነ የማትታወቅ የቴዎድሮስ፣ የሚኒልክና የኃይለ ሥላሴዋ ኢትዮጵያ ብሎ ሲያንቋሽሽ ከርሞ አሁን ለምን ሽር ጉድ ለማለት ፈለገ? የውድ ሀገራችን ሐውልት ባንዳ አባቶቹ ለፋሽስት ያስረከቡትን የአክሱም ኃውልት ፋሽስት ቢመልስ፤ እንግሊዞች ገናናውን ንጉሠ ነገሥት አፄ ቴዎድሮስ ገድለው፤ ለሶስት ሺህ ዘመን ተከብሮ የኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘውድ፣ ቤተክህነታትና መስጊዶች ቅርፃ ቅርፆችን ዘርፈው፤ ልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስን ጠልፈው፣ የኢትዮጵያን ሠራዊት ፈጅተው፣ አገራችንን ካዋረዱ በኋላ ዛሬ ለአቶ መለስ የአለማየሁን አጥንት ለበረከት ቢያቀርቡ የኛ ደስታና ፍንጠዛ ከምኑ ላይ ነው? እሱ ቀማኛ እንግዴ ልጁ ቅቤ አንጓች ዳኛ አይሆንብንም ወይ? የአላህ ሙዱ ካድሬ ጫት አላምጦ ቢያብጥ፣ በማሕሙድ ሰለሞን ቢተካ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን የሚሳስጨፍረው ጉዳይ አገኘ። የአንድ መቶ ሺህ የኢትዮጵያ ወጣት ደም በባድሜና በሞቃዲሹ በከንቱ ፈሶ፣ ባድሜ ለሻዕቢያ ስትሰጥ መለስ ያገኘው ስብሃትና በረከት ፀሐይ ሞቅ ሲላት የኢትዮጵያ ስዩመ መሳፍንትነቱ ከንቱ ውዳሴ አይደለምን?

በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ) ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለኢትዮጵያ ወዳጆች እንዲሁም ለቅንጅት አመራርና አባላት የሚያስተላልፈው መልዕክት፣ ሻዕቢያዊ ወያኔዎች በፈፀሙት ሕገ-ወጥ አፈና ሰለባ ሆነው፣ ባልፈፀሙት የሐሰት ውንጀላ ከሁለት ዓመት በላይ በእስራት ቆይተው አሁን እንዲቀጡ የተወሰነባቸው ጀግና ዜጎች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና ሕዝብ የጣለባቸውን አደራ እንዲወጡ ነው። እነዚህ የሠላም ልዑካን እስኪፈቱ ድረስ ኢ.ብአግ አስፈላጊውን ሁሉ ትግል ለማካሄድና ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ለመተባበር ዝግጁ መሆኑን እንገልፃለን።

ድልና ዴሞክራስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ።
የወያኔ 3ፕሮግራም4 እና "constitution" ይወድማል።
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች!

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ)
ማዕከላዊ አመራር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ

P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A. •
Telephone (202) 785-1618
www.enufforethiopia.org